# aMASE: advancing Migrant Access to health Services in Europe

## (ኤ.ኤም.ኤ.ኤስ.ኢ.፧-አውሮፓ ውስጥ ለሚገኙ ስደተኞች የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽነት ማሳደግ)



የጥናት የመረጃ ቅጽ

Version 3 30.01.2012 • Amharic • Web • Questionnaire

# የመረጃ ቅጽ

## ስለ ኤ.ኤም.ኤ.ኤስ.ኢ....

ከዓለም ዙሪያ የመጡ ሰዎች አውሮፓ ውስጥ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ያገኛሉ። ከሌላ ሀገር የመጡ ሰዎች ወደ ኤች.አይ.ቪ የአገልግሎት ቦታዎች የሚሄዱት በጣም ሲታመሙ ሲሆን ይህም ለጤንነታቸው በጣም መጥፎ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ወደ አባለዘርዕ ጤናና የኤች.አይ.ቪ አገልግሎቶች ቀደም ብለው እንዳይሄዱ የሚያደርጋቸውን ነገር ለመለየት ይህን ጥናት እያደረግን ነው። ይህን መረጃ በመጠቀም በአውሮፓ ውስጥ የጤና እንክብካቤ የሚደረግላቸው ሁሉም ሰዎች የሚያገኙትን አገልግሎት ለማሻሻል እንችላለን።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### ይህን ጥናት የሚያደርገው ማን ነው?

ይህ ጥናት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት በአውሮፓ ህብረት ነው። ጥናቱ የሚደረገው ከለንደን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እና ከእስፔን ኢንስቲቲዩት ኦፍ ኸልዝ III በተወጣጡ ተመራማሪዎች ነው። ዶክተር ፊዮና በርንስ እና ዶክተር ጁሊያ ዴል አሞ ፕሮጀክቱንና ሁሉንም መረጃ በተመለከተ ሀላፊዎች ናቸው። ጥናቱ የስነ-ምግባር ማረጋገጫ ከለንደን ቤንታም የምርምር ስነ-ምግባር ኮሚቴ አግኝቷል።

### እኔ ለምን ተጠየቅሁ?

የጤና አገልግሎቶችን በተመለከተ ያለውን ጥሩና መጥፎ ነገር ለማወቅና መሻሻል የሚችለውን ነገር ለመለየት ስለጤና እንክብካቤ ያላቸውን ልምድ የሚነግሩን ከተወለዱበት ሀገር ውጪ የሚኖሩ ሰዎች እንፈልጋለን። ከ18 ዓመት በላይ ከሆኑ፣ የእርስዎ አስተያየት ለውጥ ማምጣት ይችላል።

## መሳተፍ አለብኝ?

የመሳተፍ ወይም ያለመሳተፍ ውሳኔው የእርስዎ ነው። ለመሳተፍ ከወሰኑ፣ ይህን የመረጃ ቅጽ አትመው መያዝ ይችላሉ። መስማማትዎን ለማሳወቅ ከመጠይቁ መጀመሪያ ከሚገኝ ሳጥን ላይ ምልክት እንዲያደርጉ የሚጠየቁ ይሆናል፡ በማንኛውም ጊዜ ሀሳብዎን ቢቀይሩ፣ መጠይቁን መዝጋት ብቻ በቂ ነው።

## ምን ማድረግ ይጠበቅብኛል?

በጥናቱ የሚሳተፉት የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን በተመለከተ መጠይቆችን በመሙላት ነው። በተጨማሪም የግል መረጃዎችን (ለምሳሌ ጾታዊ ግንኙነት፣ በመርፍዬ የሚወሰድ መድሃኒት) እንጠይቃለን። መጠይቁን ለማጠናቀቅ ከ15-20 ደቂቃዎች ይወስዳል።
የተወሰኑት ጥያቄዎች የግል መረጃዎችን የሚመለከቱ ናቸው። ቢመልሱት በጣም የማይመችዎት ወይም እንደማይመልሱት የሚሰማዎት ማንኛውም ጥያቄ ሊዘለል ይችላል።

## እኔ በዚህ ጥናት የሚኖረኝ ተሳትፎ በምስጢር ይያዛል?

አዎ። ሁሉም መረጃ በጥብቅ ምስጢራዊነት ይያዛል። በመጠየቁ ውስጥ የእርስዎን ማንነት የሚያሳውቅ መረጃ የማንጠይቅ በመሆኑ ከሚሰጡት መልስ በመነሳት ማንነትዎን መለየት አይቻልም። ሁሉም እርስዎ የሚሰጧቸው መልሶች ከማን እንደሆኑ የማይታወቁና ጥበቃ የሚደረግላቸው ናቸው።

## የጥናቱ ውጤት ምን ይሆናል?

ውጤቱ በአውሮፓ ለሚገኙ የስደተኛ ማህበረሰቦች፣ ለኤን.ኤች.ኤስ እና ለእርስዎ ማህበረሰብ ጤናና ደህንነት ቁርጠኛ ለሆኑ ድርጅቶች የሚጋራ ይሆናል። በተጨማሪም፣ በትምህርታዊ ህትመቶች መውጣት እንዲችል ሆኖ ይጻፋል። እርስዎም የሚፈልጉ ከሆነ፣ የጥናቱ ውጤቶች ግልባጭ ከተመራማሪ ቡድኑ ማግኘት ይችላሉ።

## ችግር ቢያጋጥም ምን ማድረግ ይቻላል?

ስጋት ወይም ጥያቄ ካለዎት፣ ቀደም ብለው ሚስ ኢቢደን ፋኮያን (Ms Ibidun Fakoya) ቢያነጋግሩ በምትችለው መጠን ጥያቄዎን ለመመለስ ትሞክራለች። የምትገኝበትን ዝርዝር በተመለከተ ከዚህ የመረጃ ቅጽ መጨረሻ ላይ ማግኘት ይችላሉ።
የማያስደስትዎ ነገር ቢኖርና ቅሬታ ለማስገባት ቢፈልጉ፣ የሚከተለውን ቁጥሮቸቸ በመጠቀም ለጥናቱ የምርምር ስፖንሰር አስተዳዳሪ በሆነው በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ለንደን አማካኝነት ቅሬታዎን ማቅረብ ይችላሉ፡- 020 7380 9937፣ የሚጠቀሰው ሪፈረንስ 11/0237። ሁሉም ግንኙነቶች በጥብቅ ምስጢራዊነት የሚያዙ ናቸው።

Centre for Sexual Health & HIV Research, University College London, 3rd Floor, Mortimer Market Centre, London WC1E 6JB •Tel: +44 (0)20 3108 2078 • Fax: +44 (0)20 3108 2079

## ተጨማሪ መረጃ

ነጻ መረጃ፣ ምክርና እገዛ ለማግኘት ወይም በዚህ ጥናት ስለተነሳ ጉዳይ የሆነ ሰው ለማነጋገር፣ ለምርምር ቡድኑ ኢሜይል ለመላክ ወይም ከዚህ ከተዘረዘሩት ድርጅቶች ጋር ለመገናኘት አያመንቱ።
http://www.amase.eu/wp/organisations/

## በዚህ ጥናት ለመሳተፍ በማሰብ ለአሳለፉት ጊዜ በጣም እናመሰግናለን

ይህን ጥናት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት
ዶክተር ፊዮና በርንስ (0203 108 2078) ⁜ ሚስ ኢቢደን ፋኮያ(0203 108 2078) ማነጋገር ይችላሉ

Centre for Sexual Health & HIV Research, University College London, 3rd Floor, Mortimer Market Centre, London WC1E 6JB •Tel: +44 (0)20 3108 2078 • Fax: +44 (0)20 3108 2079